# ኢህአፓ የህዝብ አለኝታ ነው!

ከጀጀቤ ታሪኩ

ወያኔ በየወቅቱ በሚፈጥረው የማደናገሪያ ታክቲክ ላይ ተመርኩዞ የራሱን የፖለቲካ ፕሮግራም ለመንደፍ የሚንደፋደፈው የፖለቲካ ድርጅት ነኝ ባይ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታየ ነው። ሆኖም ግን በየዕለቱ በሚያልቀው ህዝብ ስም የሚደረገው በተቆርቋሪነት ስሜት የተቀነበበ የአስመሳይነት ፖለቲካ ከወንጀልም ወንጀል መሆኑ ግልጥልጥ እያለ መጥቷል። አንዳንዶች መጭውን ምርጫ ከተካፈሉ የምኒልክን ቤተ መንግስት በማግስቱ ወያኔን አስወጥተው ሲቀመጡበት ይታያቸዋል። ሌሎች ወያኔን ማሸነፉን ረዘም ላለ ጊዜ ቀጠሮ ይዘውበት ላሁኑ የፓርላማውን ደሞዝ መሻማቱ ብልህነት ነው ይላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ መድህኔአለም ይይለትና ለዚህ ሁሉ ያደረሰን የተማሪው ንቅናቄ ነው ብለው ያንን ትውልድ ይረግማሉ። የራሳችን የሚሉት አማራጭ የሌላቸው በመሆኑ ኢህአፓንም፣ ደርግንም ወያኔንም እንዳገኙ ያለዘመን ልጓም፣ ያለህቅ ግንዛቤ ሁሉንም አመሳስለውና አገናኝተው በምላሳቸው ይለጥጧቸዋል። ቁምነገሩ ግን አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም - ሀገሬን ወገኔን የሚል በምንም መልኩ የወያኔን ምርጫ አዳማቂ ለመሆን ያለመከጀሉ ነው። በዘገምተኛና በተፈጥሮ ለውጥ የሚያምን ሁሉ የወያኔን መሪዎች ዕድሜ አብሮ እየቆጠረ መሰንበት የማይገባው መሆኑን መገንዘቡ ነው። ወያኔ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት የመቆየት ዕድል ካገኘ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ስሟ ተለውጦ ግዛቷም ተለውጦ ምናልባትም የፈረንጆቹ ልግስና ከተቸራት “የአፍሪቃ ቀንድ” ተብላ ስትጠራ ማየት ነው። አለዚያም በወኪሎቻቸው በኩል የአውሮጳ ሀገራት ምርት አምራች ባሮችን በየክልሉ አስቀምጠው ለቀጣይ ዘመናት ህዝቡን በእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ስር ሲያስተዳድሩት መመልከት ነው። ከዚህ ሌላም በየሀገሩ የተበተነው ኢትዮጵያዊ በያለበት ስፍራ ወዶ ተሻጭ መሆኑን አስመስክሮ ባርነቱን ሲያረጋግጥ ማስተዋል ነው። ይህ ረዥም ዕድሜ የሚለመንበት ጉዳይ ሳይሆን አብዛኛው የአሁን ጊዜ ኗሪ ሰው ሊያየው የሚችል የነገ ሀቅ ነው።

ምን መደረግ አለበት ቢባል፣ መደረግ ያለበት ቀላል ነው። እውነተኛውን የሀገርና የወገን ፍቅር ያለውን ድርጅት ካስመሳዩ ነጥሎ ማየት፣ የራሱን ጥቅም በወገንና በሀገር ጥቅም ለውጦ ከጠላት ጋር ሲፋለም የኖረውን፣ የባዕዳንን ዳረጎት አሻፈረኝ ብሎ በመቆም በህዝቡ ስቃይ ላይ ለመነገድ ፍቃደኛ ያልሆነውን፣ ገንዘብ ተቀባብሎ እውነትን በሃሰት ለመለወጥ ያልተዘጋጀውን በዚህም ምክንያት በተታላዮች ዘንድ እራሱን ለውግዘትና ለጠላቶች ኢላማ የዳረገውን ወገናዊ ፓርቲ ጠንቅቆ ማወቅ። ለህዝብ ቃል የገባውን ሳይፈፅም የማይበታተን፣ የህዝብን ሰቆቃ በህይወቱ ቆሞ ማየትን እንደ ሀጢአት የሚቆጥር፣ ስለዚህም እራሱን አሳልፎ ለእምነቱ መስዋዕት የሚሆነውን ነጥሎ ማየት አይነተኛና ዋናው ነው። በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ይህ ሁሉ ማንን እንደሚመለከት ለማወቅ አስቸጋሪ አይደለም። እንዲያውም በፅናቱና በመስዋዕትነቱ የሚኮራበት ድርጅት ኢህአፓ ነው ቢባል ከሀቅ መራቅ አይሆንም። ወያኔን ለለከፈው አጋንንት ማስለቀቂያ ጠበሉ “ኢህአፓ” ነው። ስለዚህም ነው ወያኔዎች በላያቸው ላይ የሰፈረው አጋንንት ስለማይፈቅድላቸው ኢህአፓን ደፍረው ለመቅረብ ስሙንም ለመጥራት የሚቸገሩት። ማንነቱን ቢረዱትም ድርጊቱን ቢያውቁትም ደፍረው አይናገሩትም። አንዳንድ ጠረኞች በሚል ያልፉታል፣ ነፋስ ነጠቀን ይሉለታል። ደፍረው ግን ኢህአፓ ያሉ ዕለት የያዛቸው አጋንንት ጨርቁን ጠቅልሎ ጥሏቸው ወደባህሩ ይዘልቃልና ይጠነቀቃሉ። እንኳንስ እነሱ ትናንሿም የየወንዟ ዳፍንት “ኢህአፓ” ስሙ ሲጠራ ትርበደበዳለች። ውሎዋ ከየአመድ ማፍሰሻው ከየአተላ መድፊያው

ላይ በመሆኑ የሰፈረችበት ሁሉ ኢህአፓን እንዲጠላ ታደርገዋለች። ስለጠላት በተነሳ ቁጥር ኢህአፓን ቀንደኛ ጠላቱ አድርጎ እንዲያይ ትገፋፋዋለች። አንድ ሰው አፉን ሞልቶ ኢህአፓ ጠላቴ ነው ሲል ከዚህ ሁሉ ቁርኝቱ ጋር ነው ማያያዝ የሚቻለው። ኢህአፓን በጠላትነት ለመፈረጁ አጥጋቢ ምክንያት የማይሰጠው ሰው ኢህአፓ ጠላቴ ነው ብሎ ካለ ምክንያቱ ከዚህ የተለየ ነው ብሎ ማመን ያዳግታል።

ታዲያ! ከዚህ አይነቱ የቅዠት ህይወት መላቀቅ የሚቻለው እምነትን ቅድስናን ተገን በማድረግ ነው። ከአጋንንት ተጠግቶ ከሰይጣን ተቆራኝቶ የንፁህ ህዝብን ደም እየመጠጡ የዋህ መምሰል አይቻልም። እታገላለሁ ማለት፤ የህዝብ ወገን ነኝ ማለት፤ ሀገሬን እወዳለሁ ማለት፤ እነዚህን ሁሉ ሀቆች ተረድቶ ማርከሻውን መስራት ሲቻል ብቻ ነው። ኢህአፓ በቆራጥ ትግሉ፤ በህዝብ ፍቅሩ፤ መስዋዕት ከፍሎበታል። ወደፊትም እንደሚከፍልበት ጥርጥር የለውም። የህዝብ መብት እስካልተከበረ ድረስ ኢህአፓ በእያንዳንዱ የህዝብ ጠላት ደጃፍ ላይ መገኘቱን መርሳት አይገባም። ኢህአፓ በእያንዳንዱ ንፁህ ህዝብ ልብ ውስጥ አለኝታነቱን የመሰረተ ድርጅት መሆኑን ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አያስፈልግም። አሁንም ለህዝብ ፅናትን፤ አሁንም ለህዝብ እምነትንና ተግባራዊነትን እንደሚያስተምር ለማወቅ ልቦናን ከፍቶ ማስተዋሉ በቂ ነው። ኢህአፓ መሪዎቹን መስዋዕት የከፈለ ቢሆንም፤ “ግንባርህን አሳያቸው” ብሎ፤ “የናንት ምጣት በዝቷል እኛ ነን እምንመጣ እያለ” ለጠላቶቹ የምስራች ነጋሪ በሆኑ ወጣቶች ታጅቦ ለትግሉ መሰለፉን ለመረዳት ለታቦታት “ግምጃ” አስገባለሁ ብሎ መሳል አያሻውም። ኢህአፓን ለማጥፋት ማሰብ ኢትዮጵያን እንደማጥፋት መክበዱን ለመረዳት የዕድሜ ባለፀጋ መሆንን አይጠይቅም። የኢህአፓን ስም ለማጥፋት ለማቆሸሽ የሌለ ወንጀል በመለጠፍ ከህዝብ ለመለየት የሚሯሯጡት የባዕዳን ቅጥረኞች ሌላ ተልዕኮ የላቸውም። ተልዕኮቸው ህዝባዊ ፍቅርና አመኔታ ያለው ድርጅት በሀገሪቱ እንዳይኖር ለማድረግ ነው። ህዝቡን አለኝታ ለማሳጣት ነው። ይህ ደግሞ በአንፃሩ ለአወናባጆች ለአስመሳዮች መንገድ የከፈተ ቢመስልም፤ በአንፃሩ ህዝብ እውነቱን እንዲረዳው ረድቶታል።

ህዝብና የኢህአፓ ዓላማ፤ ህዝብና የኢህአፓ ህልውና አይነጣጠሉም። በምላሳቸው ህዝባዊ ለመምሰል የሞከሩ ሁሉ ድርጊታቸው ማንነታቸውን አጋልጦታል። ፅናቱን ይዞ የህዝብ አለኝታነቱን አስከብሮ ላለፉት አርባ አመታት የጠላትን ደባ ሁሉ እየተቋቋመና ሴራቸውንም እያከሸፈ የተጓዘው ኢህአፓ አሁንም በህዝብ ቁርጠኛ መብት ላይ ያላወላዳ አላማውን ይዞ እንዲዘልቅ የታወቀ ነው። ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል እንዲሉ በመሆኑ፤ ዛሬ ለትግል በቁርጠኝነት ከሚሰለፈው ይልቅ በባዕዳን የማደናገሪያ ምልጃ የሚዋዛው ወገን አመዝኖ መገኘቱ በግድ እንደ ኢህአፓ ያሉ ለህዝብ ታማኝና የትግል ተመክሮ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ግምባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ይጋብዛል። ምንም እንኳ የህዝብን ስሜት እያዳመጠ የሚጓዝ ድርጅት መጥፋቱ ቢያሳዝንም። በእርግጥም እንደ ኢህአፓ ያሉ ተመክሮ ያላቸው ድርጅቶች በህዝብ ታቅፈው እስካሉ ድረስ፤ ኢትዮጵያ ከመጨረሻው የውድቀት ምዕራፍ ላይ ደረሰች ሊባል አይቻልም። የመጨረሻው ምዕራፍ ለማንም ቢሆን የማይበጅ ወቅትን የሚጋብዝ ነውና። ሀቀኞች እውነተኛ የህዝብ ወገኖች በወያኔ ላይ ለሚወሰደው የፖለቲካ ትግል ሁሉ መሰናክል ከመፍጠር መቆጠብ ይገባቸዋል። ለዚህ ተግባር መቆም ያለባቸው የኢህአፓ አባሎችና የኢህአፓ ገድል አድናቂዎች ብቻ መሆን አይኖርባቸውም። የህዝብ ብሶት ተቆርቋሪዎች፤ የሀገር አፍቃሪዎች - በኢህአፓ ላይ ስለሚወረወረው ድንጋይ የበኩላቸውን ማለት ይጠበቅባቸዋል። “ወኔ ካላችሁ ድንጋዩን በወያኔ ላይ አውሉት አለበለዚያ በአጎብዳጅነት ለመስራት ለምታስቡት ህንፃ ይረዳችሁ ይሆናልና ከበር-አፋችሁ አጠራቅሙት” “ኢህአፓን ለቀቅ ወያኔን ጠበቅ” ብሎ ምክርን መለገስ ያስፈልጋል። ኢህአፓንም ለጠላት ወሬ ቁብ ሳትሰጥ ዛሬም እንደጥንቱ አልገዛም፤ አልንበረከክም ባይነትህን ሙጥኝ ብለህ፤ ባዮችንም አበራክተህ በድል ጎዳና ተጓዝ ብሎ ድጋፍን መስጠት ግዴታ ይሆናል። ይህ አይነቱ ወገናዊ ምክር ሀገርን ለማዳን ለሚደረገው

ትግል የሞራል ዋጋው ከፍተኛ ነው። ህዝብ ብቻውን እንዳልሆነ ከጎኑ የማይለዩ እንደ ኢ.ህአፓ ያሉ ታማኝ ድርጅቶች መኖራቸውን ይመሰክርለታልና። "አሉ በርክክ በርክክ አውሬ መስያቸው - ሰው ያለኝ መሆኑን ማን በነገራቸው!" ብሎ እንዲዘምር ለህዝብ ምክንያቱ ይሆናሉና።

ቸር ይግጠመን!